# ታላቁ የሐይማኖት መሪና አርበኛው ኢትዮጵያዊ አባታችን አባ መልአከ ሰላም ሲሳይ አየለ ይመር በ80 ዓመታቸው አረፉ




**ሚያዝያ 13 ቀን 1919 ዓ.ም. - ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ.ም.**

ታላቁ አባታችን አባ መልአከ ሰላም ሲሳይ አየለ ይመር የኃያሉ መድኃኔ ዓለም አገልጋይ፤ ቆራጡ የተዋሕዶ ልጅ፤ የነፃነት ታጋይ አርበኛ፤ የቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ልጅ፤ በኮለምበስ ኦሃዮ የሚገኘው የደብረ መድኃኒት መድኃኔ ዓለም ካቴድራል መሥራችና አስተዳዳሪ እንዲሁም በስደት የሚገኘው ህጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ገንዘብ ያዥ በደረሰባቸው ሕመም ለ5 ወራት በተለያዩ ሆስፒታሎች በሕክምና ሲረዱ ቆይተው በተወለዱ በ80 ዓመታቸው ዓርብ ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ.ም. ከሚወዷቸው ውድ ልጆቻቸው፣ ከሚያፈቅሩትና ለረጅም ዓመታት በአባትነት ካገለገሉት ሕዝበ ክርስቲያን ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

<u>የቀብር ሥነ-ሥርዓት ፕሮግራም፦</u>

- ከሰኔ 23 ቀን ጀምሮ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ፓትሪያርክ ርዕሰ ሊቃነ-ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ብፁዓን አባቶች፣ አበው ካህናትና የክብር እንግዶች ኮለምበስ፣ ኦሃዮ መግባት ጀምረዋል።
- ከሰኞ ሰኔ 25 ቀን ጀምሮ ጠዋት ከ6፡00 AM እስከ 7፡00 AM እንዲሁም ማታ ከ5፡30 PM እስከ 7፡00 PM ፀሎትና ትምህርት ይሰጣል።
- ረቡዕ ሰኔ 27 ቀን ከ10፡00 AM ጀምሮ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ፓትሪያርክ ርዕሰ ሊቃነ-ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራ ቅዳሴና ፀሎተ-ፍትሐት ይካሄዳል።
- ቅዳሜ ሰኔ 30 ከጠዋቱ 9፡00 AM እስከ 10፡30 AM በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ የሚመራ የመጨረሻ ፀሎተ ፍትሐት በደብረ መድኃኒት መድኃኒዓለም ካቴድራል ከተካሄደ በኋላ አስከሬኑ ከደብረ መድኃኒት መድኃኔ ዓለም ካቴድራል ተነስቶ ወደ ተዘጋጀው የቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን የቀብር ቦታ ይሸኛል።
- የቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን መቃብር አድራሻ፡
  - St. Joseph Cemetery<br>644 South High Street<br>Columbus, OH 43137 ስልክ: 614-491-2751
- የደብረ መድኃኒት መድኃኔ ዓለም ካቴድራል አድራሻ፦
  - Debre Medhanit Medhane Alem Cathedral<br>610 Neil Avenue<br>Columbus, OH 43215 ስልክ: 614-280-0626
- ለተጨማሪ መረጃ:
  - 614- 622-5922 ወይም 614-332-8002 ወይም 614-989-4777

